# በጀርመን የኢትዮጵያውያን የጋራ መድረክ
# ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ
## የአv ም መግለጫ

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአምባገነኑ የህወሓት/ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ አስከፊ የአገዛዝ ሥርሃት ውስጥ ከወደቀ አስራ አምስት የስቃይና የመከራ ዓመታትን አስቆጠረ:: በነዚህ ዓመታት ውስጥ በሥልጣን ላይ በጠመንጃ ኃይል ያለው ገዢው ፓርቲና መንግሥት በአገሪትዋ ብሔራዊ ልህልናና በሕዝባችን ላይ የፈጸማቸው ዘግናኝና አሰቃቂ የሰብሃዊ መብት ረገጣዎች በቀላሉ ታይተው የሚታለፉ አይደሉም::

አፋኝና ፈላጭ - ቆራጭ የሆነው የህወሓት/ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንግሥት ገና ጠዋት ከጅምሩ ከጫካ ወጥቶ ቤተመንግሥት ሲገባ አፍራሽ መንግሥት ለመሆኑ ድርጊቶቹ ሁሉ ሕያው ምስክሮቹ ናቸው:: ከአፍራሽ ተፈጥሮሃዊ ባህርዩ ጥቂቶቹን እን^ን ለአብነት ብቻ መጥቀስ ቢያስፈልግ በህወሓት የርዕዮተ ዓለም መሪ ተዋናይ በሆኑት በጨካኙ በአቶ መለስ ዜናዊና ግብረ አበር መሰል ካድሬዎቹ አማካይነት ስለ ዴሞክራሲ እያወሩ ሕዝብን ማፈንና ረግጦ መግዛት፣ ስለ ሠላም እየዘመሩ የጦርነት ክተት አዋጅ ከበሮሃቸውን መደለቅ፣ ስለ ሙስና አዋጅ እያወጁ በነዚህ አጭር ዓመታት ውስጥ የሕዝብ ሃብትና ንብረትን አላግባብ እያዘረፉ የፋይናንስ መሣፍንቶችን መፈልፈል፣ ስለ ሕግ የበላይነት እየለፈፉ ራሳቸውን ፈፅሞ ከሕግ በላይ ማኖር፣ ስለ እኩልነት እየደሰኮሩ ጭፍን የብሔረሰብ አድልዎ መርዝን መርጨት፣ ስለ ፕሬስ ነፃነት እየቀባጠሩ ሐቀኛ የሕዝብን ድምፅ አስሚ ጋዜጠኞችን ለወከባና ለስራት መዳረግ፣ ስለ መድበለ ፓርቲ አመራር እየለፈለፉ የአንድ ወጥ የጎሳ ፓርቲ የበላይነት እንዲነግስ ምቹ ሁኔታዎችን የሚያስተካክሉ አልፎ ተርፎም በአገሪትዋ ላይ ግርግርንና ሽብርተኝነትን ለማስፋፋት የሚጣደፉ ለመሆናቸው ባለፉት የአገዛዝ ዓመታትና ዛሬም በተግባር ላይ እየዋሉ መሆናቸውን በዓይነ - ሕሊናችን የታዘብናቸው ዓበይት የገዢው ፓርቲና መንግሥት ፖለቲካዊ አመራር ቀውስ ምልክቶች ናቸው ::

በተለይም ግንቦት 7 ቀን 1997ዓ.ም ከተካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብ ተወካዮች ምርጫ ወዲህ የህወሓት/ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ድብቅ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ባህርዩ ገሃድ ወጥቶአል:: „ንጋትና ጥራት እያደር ይታያል“ የተሰኘው የብሂሎች አባባልም በወያኔ ተፈጥሮሃዊ ባህርዩ ውስጥ በይፋ በሰኔ 1 ቀን 1997ዓ.ም እና ከጥቅምት 22 ቀን 1998ዓ.ም ጀምሮ „ የምርጫ ድምፄ ይከበርልኝ !“ ብለው ብሶታቸውን ለማሰማት በአዲስ አበባ ከተማ አደባባይ በወጡ ንጹሃን ዜጎች ጥያቄ ላይ ምላሹ ፋሽስታዊ የግፍ ጭፍጨፋ፣ ግርፋት፣ የጅምላ አፈናና እስራት፣ አልፎ ተርፎም ለስደት መዳረግ መሆኑን በጥሞና ተገንዝበናል::

በአገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ላይ በደሴ፣ በጅማና በጎንደር፣ በደብረ ብርሃን፣ በባሕር ዳር፣ በአዋሳና በአርባ ምንጭ፣ በመቀሌ፣ በአምቦና ድሬዳዋ...ወዘተ አረመኔያዊው የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንግሥት የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎችን እንዲፈታ በተማሪዎች የሚካሄደው አመፅም የዚሁ ትግል አካል መሆኑን ለመረዳት ችለናል:: ያለነው ሰብሃዊ መብት ያለምንም ርህራሄ በሚረገጥበት ወቅት ላይ ነን :: የሕዝባችን የሠላማዊ ተቃውሞ በሩም ጥርቅም ብሎ ተዘግቶአል :: የፕሬስ ነፃነቱም ተዳፍኖአል ::

ዛሬ የአምባገነኑ ህወሓት/ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ፖለቲካዊ አመራር እርቃነ ሥጋውን ቀርቶአል :: ተፈጥሮ ከህንሰሳ እንዲለይ የሰጠውን የማሰብና የማስተዋል ሥነ-አዕምሮውን አጥቶ የጫካ አውሬነቱን በግልፅ በማሳየት፣ ሥልጣንን በሕዝብ ምርጫ ማግኘት ተስኖት በጠመንጃ አፈሙዝ አፍኖ ለመግዛት እና ዳግም ለአምስት ዓመት በነደፈው የክህደት ቁልቁለት ጎዳና ላይ ለመገስገስ በሕልምና ቅዠት ውስጥ ይገኛል :: በተባበረ ሕዝባዊ ትግል ኃይል የወያኔ/ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ከበትረ-ሥልጣናቸው ተሸቀንጥረው ሊወድቁ በሚችሉበት የገደል አፋፍ ላይ መቆማቸውንና ግብሃተ-መሬታቸው የተቃረበ መሆኑን ለመረዳት በፍፁም ተስኖአቸዋል :: የአሣ ግማቱ ከጭንቅላቱ ይሉዋችኋል ይኼ ነው :: በአንድ ወራጅ ውኃ ሁለት ጊዜ መሻገር እንደማይቻል ሁሉ ኢዴሞክራሲያዊውን የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንግሥትንም በ 15 ዓመታት የሥልጣን ላይ ቆይታው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተግባር ፈትኖታል:: መልሱም „ በቃኝ ! እምቢ ! ከንግዲህ ወያኔ አይገዛኝም ! „ ነው ::

በሥልጣን ላይ ያለው የገዢው ፓርቲና መንግሥት ሥርሃቱ የተጠላው ቀጥተኛ የግፉና የስቃዩ ተቀባይ በሆነው በአገር ውስጥ በሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻም ሣይሆን በመላው ዓለም በሚገኙ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያውያኖችም ጭምር ነው::

ስለዚህ እኛ  በጀርመን የምንገኝ አገር ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን ሚያዝያ 7 ቀን 1998 ዓ.ም በፍራንክፈርት ማይን ከተማ ቦናሜስ ላይ በተካሄደው ታላቅ ሕዝበዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተን በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካዊ ሁኔታ ላይ ሰፊ ውይይቶችንና የኃሳብ ልውውጦችን ካደረግንበት በኃላ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ባለ ዘጠኝ ነጥቦች የአ∨ም መግለጫችንን አስተላልፈናል ::

1ኛ/- ለሕዝባችን ነጻነት ሲሉ በአምባገነኑ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንግሥት የታሰሩት የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅትና የሙያ ማኅበራት መሪዎች፣ የነጻ ፕሬሱ ጋዜጠኞችና አሳታሚዎች፣ የሰብሃዊ መብት ተከራካሪዎችና የሕግ ባለ ሙያዎች እንዲሁም ደጋፊዎቻቸው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸ^ይ እንዲፈቱ :: በተጨማሪም ያለ ፍርድ የታሰሩት የሕሊና እስረኞች በሙሉና በጅምላ በግፍ የተጋዙትም ንጹሃን ዜጎች ጉዳያቸው ተጣርቶ በአስቸ^ይ እንዲለቀቁ ::

2ኛ/-በሰኔ 1 ቀን 1997ዓ.ም እና ከጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በኃላ „የሕዝብ ድምፅ ይከበር!“ ብለው በተነሱ ሰላማዊ ሰዎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በአደባባይ በፋሽስቱ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ታማቂ ፖሊሶች የተፈጸመውን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ እያወገዝን፣ ስለተካሄደው ጭፍጨፋ የሚያጣራ በተባበሩት መንግሥታት ጥላ ሥር አንድ ዓለም-አቀፋዊ አጣሪ ኮሚሽን ተ∨ቁም እንዲያጣራና ገዳዮች ለፍርድ እንዲቀርቡ እንዲደረግ ::

3ኛ/- የታሰሩ ተማሪዎችና መምህራን በአስቸ^ይ እንዲፈቱ :: ፋሽስቱ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንግሥትም እየወሰደባቸው ያለው ግልፅ ጥቃት በአስቸ^ይ እንዲቆም ::

4ኛ/- አምባገነኑ የወያኔ/ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንግሥት ለዴሞክራሲ ለውጥ በሚታገሉ ሃይሎች ላይ የሚያካሂዱትን ግድያ፣ አፈና፣ ወከባ፣ እስራትና እንግልት እንዲሁም ሕዝባችንን ማስፈራራት በአስቸ^ይ እንዲያቆሙ::

5ኛ/- የዚህ ሁሉ ግፈኛ አገዛዝ ቁንጮ የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ ከሥልጣናቸው እንዲወገዱ ::

6ኛ/- በቅርቡ የመገናኛ ብዙኃን ድህረ-ገፅ ለሕዝብ እንዳይዳረስ የተወሰደውን የመንግሥት እርምጃ በማውገዝ በአስቸ^ይ እንዲለቀቅ ::

7ኛ/- አምባገነኑ የወያኔ/ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንግሥት ለይስሙላ ባ∨∨መው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ተለጣፊ የሆኑ የቅንጅትና የኦብኮ ድርጅቶችን የመፍጠር ሂደትንና እንዲሁም ተለጣፊ ቅንጅትን አ∨ቁሞ የአዲስ አበባ ም/ቤትን ለመረከብ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በሙሉ የምናወግዝና በፍፁም የማንቀበለው መሆንችንን እንገልጻለን::

8ኛ/- ሕዝባችን በአገር ውስጥና በውጭ አገር የጀመረውን ሠላማዊ ትግል በፅናት እንዲቀጥል::

9ኛ/- እኛ በጀርመን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በጋራ መድረኩ ዙሪያ ተሰባስበን በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚካሄደው „የነፃነት፣ የዴምክራሲ ለውጥ፣ የሰብሃዊ መብት መከበር“ ትግሉ እንዲቀጥል ሕዝባዊ ጥያቄያችንን በድል እስከምንወጣ ድረስ የሚፈለግብንን ዜግነታዊ ግዴታ ለመወጣትና እስከ - መጨረሻው ድረስ ሁለገብ ድጋፍ ለመስጠት ቃል እንገባለን ::

ኢትዮጵያና ታሪ^ አይካድም !!
የታሪ^ም ጠባቂ እኛ ትውልድ እንሆናለን !!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንጊዜም አሸናፊ ነው !!

በጀርመን የኢትዮጵውያን የጋራ መድረክ ጊ/አ/ኮሚቴ
ፍራንክፈርት ማይን / ጀርመን /
ሚያዝያ 7 ቀን 1998 ዓ.ም/ አፕሪል 15.2006 እ.ኤ.አ. /